# **አዋጅ ቁጥር-----------/2014**

## የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የግብርና ምርትን ጥራት፣ የአመራረት ቅልጥፍናንና ተወዳዳሪነት እንዲሁም የግብርና እና አግሮ-ኢንዱስትሪ ተመጋጋቢነት በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ወሳኝ በመሆኑ፤

የግብርና ምርት አምራቾች ለገበያ የሚሆን የግብርና ምርቶችን ወደ ማምረት በማሸጋገር የግብርና ምርቶችን ከሚያዘጋጁ፣ ከሚያቀነባብሩ፣ እሴት ከሚጨምሩ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከትላልቅ ገዥዎች ጋር ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር መፍጠር ወሳኝ በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ያሉት ሕጎች የግብርና ምርት ውልን ልዩ ባሕሪያት በተሟላ መልኩ የማያስተናግዱ በመሆናቸው፤ የግብርና ምርት ውልን በመጠቀም ማምረት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ የእውቀትና ክህሎት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት የአምራች እና የአስመራች ግንኙነት በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ የሚመራበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 55(6) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### **ክፍል አንድ**

### **ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር---/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1/ "የግብርና ምርት" ማለት በጥሬው ተመርቶ እና ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የእጽዋት ምርት፣ ፣የመኖ፣የእንስሳት፣ የዓሳና የሀር ምርትና ዘር ነው፤

   2/ "እንስሳት'' ማለት የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ፍየል፣ የጋማ ከብት፣ ግመል፣ ዶሮ፣ ንብ፣ ዓሣ፣ የሐር ትል፣ አሳማ፣ ሌሎችና እና ወደፊትም ሊላመዱ የሚችሉትንም ያጠቃልላል፤

   3/ "ዕፅዋት ": ማለት የብርዕ፣ የአገዳ፣ የቅባት፣ የጥራጥሬ፣የአትክልት፣ የፍራፍሬ፣የስራስር፣የቅመማቅመም፣የአነቃቂ ሰብሎች፣የኢንዱስትሪ ሰብሎች፣ ደንና የደን ውጤቶች እና ሌሎችንም ያጠቃልላል፤

   4/ "የግብርና ምርት ውል" ማለት በግብርና ምርት አምራች እና አስመራች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

   5/ "አስመራች" ማለት የግብርና ምርት ለማስመረት ከአምራች ጋር ውል የሚገባ ሰው ነው፤

   6/ "አምራች" ማለት የግብርና ምርት ለማምረት ከአስመራች ጋር ውል የሚገባ ሰው ነው።

7/ "የተቀናጀ የአምራችና አስመራች ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች የራሱ ይዞታ ኖሮት በማምረት ተግባር የተሰማራ ነገር ግን የሚፈልገው የምርት መጠን በቂ ባለመሆኑ በዙሪያው ካሉ አነስተኛ ይዞታ ካላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ከሌሎች ፈቃድ ካላቸውና በግብርና ምርት ማምረት ከተሰማሩ ባለሃብቶች ጋር የሚያደርገው ስምምነት ነው፤

8/ "የተማከለ ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች የራሱ የሆነ የማምረቻ ይዞታ ሳይኖረው ማምረትም ተግባር ውስጥ ሳይገባ ከአምራቹ ጋር የሚያደርገው ስምምነት ነው፤

9/ "የባለብዙ ተዋንያን ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች እና አምራች በበጎ ፈቃዳቸው በሶስተኛ ወገን ድጋፍ እና ማስተባበር የሚከናወን የግብርና ማስመረት ስምምነት ነው፤

10/ የአገናኝ ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ በአምራቹ ፈቃድ ማንኛውም ሰው አምራቹን ወክሎ ከአስመራቹ ጋር የሚያደርገው ስምምነት ነው፤

11/ "ሦስተኛ ወገን"፡ ማለት በአስመራችና በአምራች መካከል በሚካሄድ የግብርና ምርት ውል ሂደት ድጋፍ የሚሰጥ ሰው ነው፤

12/ "ግብዓት"ማለት የግብርና ምርት ማሳደጊያ የሚውል ምርጥ ዘር፣ማዳበሪያ፣ ፀረ ተባይ ፣ ፀረ አረም፣የቴክኒክ ድጋፍ፣ የፋይናንስ አቅርቦት እና ሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ያካትታል

13/ "የቴክኒክ ድጋፍ" ማለት የግብርናን ምርትን በማምረት ሂደት የሚጠይቀውን የዕውቀትና የክህሎት ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ነው፤

14/ "አግባብ ያለው አካል" ማለት አዋጁን እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎች ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የግብርና ሚኒስቴር ወይም በክልል ግብርና የሚመለከተው የመንግስት ተቋም ነው፤

15/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

16/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ፣ድሬዳዋ አስተዳደርን እና የተመሰረቱትን አዲስ ክልሎች ይጨምራል፤

17/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

18/ በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በማንኛውም የግብርና ምርት ውል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል"።

## ክፍል ሁለት

## የግብርና ምርት ዉል መነሻ ሃሳብ አቀራረብና ይዘት

4. <u>አቀራረብና የድርድር አግባብ</u>

1/ የግብርና ምርት ውል አመሰራረት የሚጀምረው አስመራቹ ወይም አምራቹ በሚያቀርበው የዉል ሃሳብ መነሻነት ሊሆን ይችላል፤

2/ የግብርና ምርት ውል መነሻ ሃሳብ በፅሁፍ ወይም በቃል ሊቀርብ ይችላል፤

3/ የውል የመነሻ ሃሳብ የምርቱን አይነት፤ ዋጋን፣ የአከፋፈል ሁኔታን፣ መጠንን፣ የጥራት ደረጃን፣ የጊዜ ገደብን፣ የማከማቻ መጋዘንን፣ የማስረከቢያ ቦታን፣ የሚያስፈልግ ድጋፍን፣ የክትትልን እና ሌሎች የተዋዋዮች ውሳኔ ሊደግፉ የሚችሉ መረጃዎች ይጨምራል፤

4/ የውሉ ሃሳብ የቀረበለት ወገን የውሉን ሁኔታዎች በአግባቡ ለመመርመር በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፤

5/ በግብርና ምርት ውል ድርድር ሂደት ተዋዋይ ወገኖች በሶስተኛ ወገን እገዛ ሊደረግላቸው ይችላል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀዉ ቢኖርም ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ወይም መንግስታዊ ያልሆነ የልማት ድርጅት የግብርና ምርት ዉልን አስመልክቶ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ሃሳብ ማቅረብ ወይም ማመቻቸት ይችላል፤

5. <u>የግብርና ምርት ውል አዘገጃጀት</u>

1/ የግብርና ምርት ውል  በማያሻማ ሁኔታ በፅሁፍ መዘጋጀት አለበት፤
2/ ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርት ውላቸውን በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ቢያንስ አንዱ የክልሉ የሥራ ቋንቋ መሆን አለበት፤
3/ ውሉ ከአንድ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ የትርጉም ልዩነት ሲከሰት ውሉ የተፈጸመበት ክልል የሥራ ቋንቋ ትርጉም ገዥ ይሆናል፤
4/ የግብርና ምርት ውል ቢያንስ በሦስት ምስክሮች ፊት መፈረም አለበት። ከምስክሮች አንዱ አግባብ ያለው አካል ተወካይ ሊሆን ይገባል፤
5/ የግብርና ምርት ውል ውል ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ አለበት።፤
6/ ውሉ ከግብርና ምርት ውል ድንጋጌዎች ውጪ ሌሎች ሰነዶችን የሚጠቅስ ሲሆን የተጠቀሱት ሰነዶች ከተፈረመ የውሉ ቅጂ ጋር የውሉ አካል ሆነው ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ለተሰጠው አካል መቅረብ አለባቸው።

6. <u>የግብርና ምርት ውል ይዘት</u>

የግብርና ምርት ውል ቢያንስ የሚከተለው ይዘት ሊኖረው ይገባል።

1/ የአምራቹ እና የአስመራቹ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣
2/ የኢንቨስትመንትና የንግድ ፈቃድ ቁጥር
3/ የግብርና ምርት ውሉ ዓላማ፣
4/ የማሳው ወይም የማራቢያ ቦታ ስፋትና አዋሳኞች ወይም የሚራባዉ ብዛት
5/ የአምራቹ እና የአስመራቹ መብትና ግዴታዎች፣
6/ የምርት አይነት፤ ጥራትና የመጠን መግለጫ መስፈርቶች፣
7/ የግብዓት እና የምርት ዋጋ አወሳሰን፤
8/ የማጓጓዣ ሥርዓትና የወጪ አሸፋፈን
9/ የቴክኒክ ድጋፍ ዓይነቶች፤
10/ እንደ አግባብነቱ የአዳቃዮች እና የአዕምሮ መብት ባለቤትነትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች፣
11/ ውሉ እንዳይፈጸም ማድረግ የሚችሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች
12/ ተዋዋይ ወገኖች ወራሾች ወይም ተተኪዎች መብትንና ግዴታን ስለማስተላለፍ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣
13/ የግብርና ምርት ውሉ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ፤ ስለሚሻሻልበት ወይም ስለሚቀየርበት፤ ስለሚቋረጥበት ሁኔታዎችና ሥነ-ስርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣
14/ አለመግባባቶችን መፍቻ መንገዶች፤
15/ በምርት ውሉ መሰረት የምርቱ ጥራትና መጠን በመቀነስ ወይም በመጨመር ልዩነት ቢፈጠር የዋጋ ሥሌት ማስተካከያ ስለሚደረግበት፣
16/ የግብርና ምርት ውሉ የተፈጸመበት ጊዜና ቦታ።

## ክፍል ሦስት

## የግብርና ምርት ውል ዓይነቶች፣ የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች

7. <u>የግብርና ምርት ውል ዓይነቶች</u>

በዚህ አዋጅ የግብርና ምርት ውል አይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ።

1/ አውትግሮወር ውል፤
2/ የተማከለ ውል፤
3/ ባለብዙ ተዋንያን ውል፤

4/ የአገናኝ ውል፤

8. **<u>የአስመራቹ መብትና ግዴታዎች</u>**

አስመራቹ የሚከተሉት መብትና ግዴታዎች ይኖሩታል፤

1/ በተሰማራበት መስክ ህጋዊ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ የማቅረብ፤
2/ በግብርና ምርት ውሉ በተመለከተው ቦታ፣ ጊዜ፣ የምርቱን ጥራትና መጠን አረጋግጦ የመረከብ፤
3/ በግብርና ምርት ውሉ መሠረት አግባብነት ያላቸውን የግብርና ግብዓቶች እና የቴክኒክ ድጋፍ ለአምራቹ የማቅረብ፤
4/ በግብርና ምርት ውሉ መሠረት ክፍያ በወቅቱ የመፈፀም፤
5/ አምራቹ መረጃ እንዲይዝ ክትትልና የቴክኒክ ድጋፍ የማድረግ።

9. **<u>የአምራቹ መብትና ግዴታዎች</u>**

አምራቹ የሚከተሉት መብትና ግዴታዎች ይኖሩታል፤

1/ ከአስመራቹ በውሉ መሰረት ማግኘት የሚገባውን ክፍያ የማግኘት፤
2/ በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ከአስመራቹ የሚሰጠውን የግብዓት ዓይነት፣ ጥራትና መጠን በወቅቱ አረጋግጦ የመረከብ እና የመጠቀም፤
3/ የቴክኒክ ስልጠናና የምክር አገልግሎት የመቀበልና የመተግበር፤
4/ በግብርና ምርት ውሉና በምክረ-ሀሳቡ መሰረት ወቅታዊ ስራዎች የማከናወን እና መረጃ የመያዝ፤
5/ የምርት ጥራት የሚያሻሽሉና ብክነትን የሚቀንሱ እርምጃዎች የመውሰድ፤
6/ በግብርና ምርት ውሉ መሰረት ምርቱን በተገለጸው ቦታ፣ ግዜ፣ ጥራትና መጠን አረጋግጦ የማስረከብ።

10. **<u>የግብርና ምርት ዋጋ፣ የክፍያ ዘዴ እና አከፋፈል</u>**

1/ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ የሚሸፈነውን የግብርና ምርት ዋጋ የማምረቻ እና ተዛማጅ ወጪዎችን ይወስናሉ፤
2/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን ጠቅላላ ዋጋ ወይም የነጠላ ዋጋ ክፍያ ስሌት በግልጽ ማስፈር አለባቸው፤
3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውል ከተገለጸው የጥራት ደረጃ በመቀነስ ወይም በመጨመር ልዩነት ቢፈጠር የዋጋ ሥሌት ማስተካከያ በውሉ በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው፤
4/ ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን ዋጋ አከፋፈል እና የክፍያ ጊዜ በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው፤
5/ በግብርና ምርት ውል የምርትና ግብይት ግንኙነትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ በምርት ርክክብ ጊዜ የምርት ገበያ ዋጋ በውል ከተገለጸው በላይ ከፍ ያለ እንደሆነ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በድርድር የዋጋ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ። ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤
6/ አስመራች በውል በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የተረከበውን የምርት ዋጋ ድምር ተቀናሽ የሚሆን የግብዓት ዋጋና ቀድሞ ለአምራች የተሰጠ ቅድመ ክፍያ ካለ ተቀናሽ በማድረግ ለአምራች በአቅራቢያው በሚገኝ ባንክ በስሙ በከፈተው የባንክ ሂሳብ በኩል ገቢ ማድረግ አለበት።

11. **<u>የግብርና ምርት መጠንን ስለመወሰን</u>**

ተዋዋይ ወገኖች፡

1/ የግብርና ምርቱን አማካይ መጠንና መለኪያ በግልፅ መወሰን አለባቸው፤
2/ በውል ከተመለከተው የምርት መጠን ለመቀነስ ወይም ለመጨመር መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶችና የውል ተፈጻሚነት ደረጃ በግልጽ ድንጋጌዎች በውሉ ውስጥ መካተት አለባቸው። ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ መመሪያ ይወሰናል፤
3/ የግብርና ምርቱ መጠንና መለኪያው በበቂ ሁኔታ ተዘርዝሮ ያልተቀመጠ እንደሆነ በድርድር ለመወሰን ይችላሉ።

12. **<u>የግብርና ምርት ጥራትን ስለመወሰን</u>**

1/ ተዋዋይ ወገኖች የምርት ጥራት ደረጃና ማረጋገጫ መንገዶችን በግልጽ ማስቀመጥ አለባቸው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምርት ጥራት መጓደል መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶችና የውል ተፈጻሚነት ደረጃ በግልጽ ድንጋጌዎች በውሉ ውስጥ መካተት አለባቸው፣ ዝርዝሩ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

3/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች እንደአግባብነቱ የማሸጊያ፣ የምርት የጥራት መግለጫ ደረጃዎችን እና የማሸጊያ ወጪዎችን ማን እንደሚሸፍን ጨምሮ በውሉ በዝርዝር ማስቀመጥ አለባቸው።

13. <u>የግብዓት አቅርቦትና ዋጋ አወሳሰን</u>

1/ አስመራቹ የሚያቀርበው የግብዓት ዓይነቶች፣ ጥራትና መጠን፣ የርክክብ ጊዜ፣ ቦታ፣ የማጓጓዣ መንገድና ዋጋ በግልፅ በግብርና ምርት ዉሉ ላይ ማስቀመጥ አለባቸው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፅዉ ቢኖርም አስመራች ለአምራች የሚያቀርበው የግብዓት ዋጋ በወቅቱ የአካባቢ ገበያ ከሚገኝ ተመሳሳይ ግብዓት ዋጋ መብለጥ የለበትም፤

3/ አስመራች ለግብዓት መግዣና ሌሎች ወጪዎች የሚሆን በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌሎች የመክፈያ አማራጮች ቅድመ ክፍያ ሊከፍል ይችላል፤ ሆኖም መጠኑ በምርት ውሉ ከተመለከተው የአጠቃላይ ምርት ዋጋ መብለጥ የለበትም።

14. <u>የግብርና ምርት ርክክብ</u>

ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን የማስረከቢያ ቦታ፤ ጊዜ፣ የማጓጓዣ ዓይነትና የወጪ አሸፋፈን መወሰን ይገባቸዋል።

15. <u>መብቶችንና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ</u>

የግብርና ምርት ውሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተዋዋይ ወገኖች፡-

1/ በውሉ ድንጋጌዎች የሚያገኙዋቸውን መብቶች ማስተላለፍ አይከለከሉም፤

2/ በውሉ ድንጋጌዎች የሚገቡቸውን ግዴታዎች ለማስተላለፍ የሚችለው የሌላኛውን ተዋዋይ ወገን ፈቃድ ካገኘ ብቻ ነው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት መብትና ግዴታ የማስተላለፍ ስምምነት ካለ ስልጣን በተሰጠው አካል በኩል መፈፀም አለበት።

16. <u>ማበረታቻ ስለማግኘት</u>

የግብርና ምርት ተዋዋዮች የመድን ዋስትናን፣ መጠነ ሰፊ የገበያ ትስስር፣ካፒታል፣ የግብር ክፍያ ቅነሳ ወይም የእፎይታ ግዜ፣የእርሻ መሳሪያዎች ድጋፍ እና ሌሎች ማበረታቻዎች በሶስተኛ ወገን ሊመቻችላቸው ይችላል። ዝርዝሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል።

## ክፍል አራት

## የግብርና ምርት ውል ግዴታዎችን መወጣት ስላለመቻል

17. <u>ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል</u>

1/ ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሊባሉ የሚችሉ ድንገተኛ ክስተቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

(ሀ) ስራውን በቀጥታ ራሱ ከሚሰራ አምራች በኩል ፅኑ ህመም፣

(ለ) ከመጠኑ ያለፈ ወይም ያነሰ ዝናብ ፣ጎርፍ፣

(ሐ) በጣም ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ሙቀት፣

(መ) እሳት አደጋ፣

(ሥ) የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ናዳ ወይም የመሬት መንሸራተት፣

(ረ) ከአምራች ግለሰቡ በተጨማሪ ተፅዕና የሚፈጥር ሰው ሰራሽ አደጋ

(ሰ) ከቁጥጥር በላይ የሆነ የእንስሳት ወይም እፅዋት በሽታና ተባይ ወረረሽኝ ክስተቶች ናቸው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ተብለው ሊወሰዱ የሚችሉት በውል በተጠቀሰው የምርት ዓይነት ላይ ያስከተሉት የጉዳት መጠን አምራቹ የገባውን ግዴታ

በውሉ መሰረት መፈጸም የማያስችለው ስለመሆኑ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ወይም አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ከሆነ ነው፤

3/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ሊባሉ የሚችሉ ክስተቶችን እና ውጤቶቻቸውን በግብርና ምርት ዉላቸው ላይ ለይተዉ ሊያስቀምጡ ይችላሉ፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) በተገለጸዉ ከግብርና ምርት ተዋዋይ ወገኖች ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በተፈጠረ ጊዜ አንዱ ለሌላው ወገን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

5/ የግብርና ምርት ውሉን ለመፈጸም ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል በተከሰተ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖች የግብዓት እና ሌሎች ወጪዎችን አሸፋፈን በተመለከተ በውላቸው ሊያካትቱ ይገባል::

18. **<u>የመድን ዋስትና</u>**

የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች:

1/ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ውሉ እንዳይፈጸም ለሚያደርጉ አደጋዎች የመድን ዋስትና ሽፋን ለመግባት ሊስማሙ ይችላሉ፤

2/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች የመድን ዋስትና ሽፋን ለማግኘት የተስማሙ እንደሆነ በስምምነታቸው የመድን አርቦን ክፍያ የመፈጸም ግዴታ የሚወስደውን ወገን መለየት አለባቸው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተገለፀዉ ቢኖርም ሦስተኛ ወገን የመድን አረቦን  ክፍያ እንዲሸፈን ሊስማሙ ይችላሉ።

## ክፍል አምስት

## የግብርና ምርት ውል ዘመን፣ ውሉን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር እና ውልን ስለማቋረጥ

19. **<u>የግብርና ምርት ውል ዘመን</u>**

1/ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ የሚሸፈነውን የግብርና ምርትን የአመራረት ዘዴ ባገናዘበ መልኩ የውል ዘመን ይወስናሉ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፅዉ ቢኖርም በባሕሪያቸው ልዩ የግብርና ምርት ውል ዘመን ለሚያስፈልጋቸው የግብርና ምርቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል::

20. **<u>የግብርና ምርት ውሉን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር</u>**

ተዋዋይ ወገኖች በሚከተሉት ምክንያቶች ውሉን ለማሻሻል ወይም ለመቀየር ይችላሉ፡-

1/ የግብዓት ወይም የምርት ዋጋ በውል ወቅት ከሚገመተው በሙብለጥ ወይም በማነስ ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ እና ይህም አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ እንደሆነ፤

2/ የግብርና ምርት ዓይነትና መጠን ለመለወጥ የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ሲኖር፤

3/ የግብርና ምርት ውል ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን ለማሻሻል ወይም ለመቀየር በሚቀርብ የጹሁፍ ጥያቄ የተስማሙ እንደሆነ በዚህ አዋጅ ስለውል መመስረት የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

21. **<u>የግብርና ምርት ውልን ስለማቋረጥ</u>**

1/ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ማቋረጥ ስለሚያስችላቸው ሁኔታዎች በግልጽ ማስፈር አለባቸው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሉን አንዱ ወገን ያለስምምነት ለማቋረጥ የፈለገ እንደሆነ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ላይ ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል አለበት፤ የካሳ ስሌትን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

**አለመግባባትን ስለመፍታት**

22. **<u>ያለመግባባት ሲከሰት የአፈታት ሂደት፦</u>**

ከውሉ ድንጋጌዎች ወይም ከውሉ ጋር በተያያዘ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ተዋዋይ ወገኖች:

1/ በመጀመሪያ አለመግባባቱን በድርድር መፍታት አለባቸው፤

2/ አለመግባባቱን በራሳቸው መፍታት ካልቻሉ አግባብነት ያለው አካል ወይም በሁለቱ ወገኖች በሚመረጥ ገለልተኛ ወገን በግልግል ዳኝነት ወይም በሽምግልና ሊስማሙ ይችላሉ፤

3/ አለመግባባቱን በግልግል ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያመለክቱ ይችላሉ። ።

**ክፍል ሰባት**

**የግብርና ምርት ውል አዋጅ አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር**

23. **<u>የሚኒስቴሩ ወይም በክልል አግባብነት ያለው አካል ስልጣንና ተግባር</u>**

1/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው አግባብ የግብርና ምርት ውሎችን በሚመለከት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

(ሀ) ለግብርና ምርት ውሎች አስፈላጊ የሆኑና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የተጠቀሱ መመሪያዎችን እና ሞዴል ውሎችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል፤

(ለ) በግብርና አምራቾች እና አስመራቾች መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር ያስተባብራል፤

(ሐ) ለአምራቾች፣ ለአስመራቾች እና ለሦስተኛ ወገን የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

(መ) ከግብርና ምርት ውሎች የሚነሱ አለመግባባቶችን አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

(ሠ) የግብርና ምርት ውሎችን ያስተዋውቃል፣ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፤

(ረ) አግባብነት ያላቸውን የተመዘገቡ ውሎችንና ሰነዶችን ይይዛል፤

(ሰ) አገራዊውን የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ተግባራትን የሚያስባብር የሥራ ክፍል ይሰይማል ወይም ያደራጃል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ለማስፈጸም ሚኒስቴሩ ከሌሎች አግባብነት ያላቸው የፌደራል እና የክልል የመንግስት አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ የልማት ድርጅቶች ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፤

3/ ሚኒስቴሩ እንደአስፈላጊነቱ ስልጣንና ተግባራቱን አግባብነት ላላቸው የፌዴራልና የክልል መንግስታት አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት በተጨማሪ በክልል ደረጃ ግብርናን አስመልክቶ ስልጣን የተሰጠው አካል እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ይህን አዋጁ ለማስፈጸም በክልል ደረጃ ህግ ሊያወጣ ይችላል፤

5/ የዚህን የግብርና ምርት ውል አዋጅ ለማስፈጸም የሚችል አግባብ ያለውን የክልል አካል የክልል መንግስት ሊሰይም ይችላል።

**ክፍል ስምንት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

24. **<u>ተፈጻሚነት ያለው ሕግ</u>**

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

25. **ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በአዋጁ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

26. **ደንብና መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን**

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

2/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም መመሪያዎችን ያወጣል።

27. **አዋጁ የሚጸናበት ቀን**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ …… / 2014 ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት